መልእክት አራት

## ለአካሉ መገንባት እና ለመንግሥቱ መሰራጨት
## ድሉን ለማሳየት
## የእግዚአብሔር ሕዝብ የጌታን ምሪት የመፈለጉ
## እና የጌታ መገኘት ያለው የመሆኑ አስፈላጊነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ማቴ. 1፡5፤ ኢያ. 6፡22-26፣ 7፡1-6፣ 10-15፣ 20-21፤ 9፡14

**I. ሁለቱ ሰላዮች ወደ ኢያሪኮ ሲመጡ፣ (ጋለሞታ እና ከነዓናዊት የነበረችው) ረዓብ ተገናኘቻቸው፣ ከእምነቷ በመነጨ ድርጊቶችም እነርሱን ለመቀበል፣ ለመሸሸግ እና ለማዳን ፈቃደኛ ነበረች (ኢያ. 2፡1-7፣ 15-16፣ 22፤ ያዕ. 2፡25)፤ በእስራኤል አምላክ አመነች፣ "አምላካችሁም እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነው"በማለት አወጀች (ኢያ. 2፡11)፡-**

ሀ. ምድሪቱን የራስ ለማድረግ ያሕዌ ጋለሞታይቱን ረዓብ ለኢያሱ አዘጋጀለት፤ በእግዚአብሔር ላይ ካላት እምነት የተነሣ "ከማይታዘዙ ጋር...አልጠፋችም" (ዕብ. 11፡31)፤ ወደ እስራኤልና ወደ አምላካቸው ዞረች፣ በእርሱና በሕዝቡ አመነች (ኢያ. 2፡12-13)።

ለ. ረዓብና ቤተሰቧ የመዳናቸው ምልክት በቤቷ መስኮት በኩል ቀዩን ፈትል ማንጠልጠሏ ነበር (ቁ. 18፣ 21)፤ በመስኮት በኩል የታሰረው ቀዩ ፈትል በምሳሌ የሚያሳየው ስለሚዋጀው የክርስቶስ ደም ግልጽ የሆነ ምስክርነትን ነው (1 ጴጥ. 1፡18-19)፤ በዚህ ምልክት እርሷና ቤተሰቧ እንደሚድኑ አምና ነበር።

ሐ. ምንም እንኳ ረዓብ የተኮነነች ከነዓናዊት እና በእግዚአብሔር ለዘላለም በተረገመው ስፍራ (ኢያ. 6፡26) በኢያሪኮ የነበረች ጋለሞታ ብትሆንም (2፡1)፤ ወደ እግዚአብሔርና ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ከዞረች በኋላ (ቁ. 22-25፤ ዕብ. 11፡ 30-31) የእስራኤል ቀዳሚ ነገድ የሆነውን የይሁዳን መሪ ልጅ ( 1 ዜና 2፡10-11) ምናልባትም ከሁለቱ ሰላዮች አንዱን ሰልሞንን አገባች (ማቴ. 1፡5)፤ ከዚያም ክርስቶስ የወጣበትን የእግዚአብሔር ሰው የሆነውን ቦዔዝን ወለደች፣ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መፈጸም በተሠጋዎው ከክርስቶስ ጋር ተዛመደች (ማቴ. 1፡5)።

መ. ይህ የሚያሳየው የኋላ ታሪካችን ምንም ቢሆን ወደ እግዚአብሔርና ወደ ሕዝቡ ከዞርን እና ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ከተገቢው ሰው ጋር ከተጋጠምን (በቁሳዊ ሳይሆን በመንፈሳዊ ትርጉም) ተገቢውን ፍሬ እናፈራለን፣ በክርስቶስ የበኵርነት ሙብት ድሰታም እንሳተፋለን—ዘጸ. 24፡13፤ 33፡11፤ ዘኁ. 27፡18፤ ዘዳ. 34፡9፤ ኢያ. 1፡1፤ 2 ነገ. 2፡2-15፤ ፊልጵ. 2፡19-23፤ 1 ቆሮ. 4፡17።

**II. ከኢያሪኮ መጥፋት በኋላ፣ እስራኤል በጋይ ተሸነፈ፤ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት በኢያሪኮ ለመዋጋት ሳይሆን ረዓብን ለማግኘት ኢያሱ ሰላዮችን ላከ፤ ነገር ግን በጋይ፣ እስራኤል የእግዚአብሔርን መገኘት ስላጣ (ኢያ. 7፡12)፤ ኢያሱ ለመዋጋት ሰላዮችን ላከ (ቁ. 2-3)፡-**

ሀ. ከሰላዮቹ ጋይን በተመለከተ ለኢያሱ የቀረበለት ዘገባ እስራኤል እግዚአብሔርን ወደ ጎን እንዳደረገው ያመለክታል፤ በጋይ ላይ ማድረግ ስለነበረባቸው ነገር እግዚአብሔርን በመጠየቅ ፈንታ እግዚአብሔርን ረሱ፣ ለራሳቸው ብቻ ግድ ተሰኙ፤ በዚያን ሰዓት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አልነበሩም፣ የጌታን ምሪት ሳይፈልጉና የጌታ መገኘት ሳይኖራቸው በራሳቸው ተንቀሳቀሱ፤ እስራኤል በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ነበር—ቁ. 1-5፣ 12፡-

1. የእስራኤል በጋይ የመሸነፍ ምሥጢር የእግዚአብሔርን መገኘት ማጣታቸውና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አለመሆናቸው ነው፤ ከዚህ ሽንፈት በኋላ ኢያሱ በታቦቱ ፊት ከጌታ ጋር የመቆየትን ትምህርት ተማረ (ቁ.6)፤ በመጨረሻ ጌታ ሊያናግረው እና ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው መጣ (ቁ. 10-15)።
2. ከዚህ ዘገባ የምንማረው መንፈሳዊ ትምህርት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆንን እኛ፣ ከእግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች—አምላክ-ሰዎች ሊያደርገን ከእኛ ጋር ብቻ ሳይሆን በውስጣችንም ጭምር ካለው ከአምላካችን ጋር አንድ መሆን እንዳለብን ነው።
3. እንደ አምላክ-ሰዎች፣ ከጌታ ጋር አንድ መሆንን፣ ከእርሱ ጋር መመላለስን፣ ከእርሱ ጋር መኖርን እና መላው ማንነታችንን ከእርሱ ጋር ማድረግን በተግባር መለማመድ አለብን፤ እንደ ክርስቲያን ለመመላለስ፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለመዋጋት እና የክርስቶስን አካል ለመገንባት መንገዱ ይህ ነው።
4. የጌታ መገኘት ካለን ጥበብ፣ ማስተዋል፣ አርቆ ማሰብ፣ ነገሮችን በተመለከተ ውስጣዊ እውቀት አለን፤ የጌታ መገኘት ለእኛ ሁሉ ነገራችን ነው—2 ቆሮ. 2፡10፤ 4፡6-7፤ ገላ. 5፡25፤ ዘፍ. 5፡22-24፤ ዕብ. 11፡5-6።

ለ. እንደ መልካሚቱ ምድር እውነታ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ ውስጥ ለመግባት፣ የራሳችን ለማድረግ እና ለመደሰት ከፈለግን፣ እንደዚያ ማድረግ ያለብን በጌታ መገኘት ነው፤ ጌታ ለሙሴ "እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፥ አሳርፍህማለሁ" ብሎ ቃል ገባለት (ዘጸ. 33፡14)፤ የእግዚአብሔር መገኘት መንገዱ፣ ሕዝቡ መውሰድ ያለባቸውን መንገድ የሚያሳይበት "ካርታው" ነው፡-

1. ለእግዚአብሔር ግንባታ ክርስቶስን ሁሉን-እንዳካተተው ምድር ሙሉ በሙሉ ለማትረፍ እና የራስ ለማድረግ ይህን መርህ መያዝ አለብን፡- የእግዚአብሔር መገኘት ለሁሉ ነገር መመዘኛ ነው፤ ምንም ብናደርግ፣ የእግዚአብሔር መገኘት እንዳለን ወይም እንደሌለን ትኩረት መስጠት አለብን፣ የእግዚአብሔር መገኘት ካለን ሁሉ ነገር አለን፣ የእግዚአብሔርን መገኘት ካጣን ግን ሁሉን ነገር እናጣለን—ማቴ. 1፡23፤ 2ጢሞ. 4፡22፤ ገላ. 6፡18፤ መዝ. 27፡4፣ 8፤ 51፡11፤ 2 ቆሮ. 2፡10፤ ሕዝ. 48፡35።
2. የጌታ መገኘት፣ የጌታ ፈገግታ ገዢው መርህ ነው፤ በእርሱ ቀጥተኛ ባልሆነ መገኘቱ ሳይሆን በቀጥተኛ እና በመጀመሪያው መገኘቱ መጠበቅን፣ መገዛትን፣ መተዳደርን እና መመራትን መማር አለብን፤ ውድ የሆነው መገኘቱ ወተትና ማር እንደምታፈሰው መልካሚቱ ምድር እውነታ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ የምንወርስበት ኃይል ነው—ዘጸ. 3፡8፤ 25፡30፤ ዘዳ. 26፡9፤ ሕዝ. 20፡6።
3. "በወጣትነቴ ድል-ነሺ፣ አሸናፊ፣ ቅዱስ እና መንፈሳዊ ለመሆን ብዙ መንገዶችን ተምሬ ነበር፤ ሆኖም ግን ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ አንዳቸውም አልሠሩም። በመጨረሻ፣ ከስልሳ ስምንት ዓመታት ልምድ በኋላ፣ ከጌታ መገኘት ውጭ የትኛውም መንገድ እንደማይሠራ አውቄአለው። እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑ ሁሉ ነገር ነው"—*Life-study of Joshua ከሚለው መጽሐፍ* ከገጽ. 48 የተወሰደ።

ሐ. እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ሲገቡና በኢያሪኮ ላይ ድልን ሲቀዳጁ፣ ኃጢአትን ያደረገው የመጀመሪያው ሰው አካን ነበረ፤ የአካን ከባድ ኃጢአት ውስጠ-መሠረታዊ፣ መንፈሳዊ ትርጉም እና መለኮታዊ እይታ ራሱን ለማሻሻል በነበረው ፍላጎቱ፣ በውጫዊ ገጽታው ራሱን የተሻለ አድርጎ ለማሳየት የሚያምር የባቢሎናውያንን (ሰናኦር ኋላ ላይ ባቢሎን ተብሎ የተጠራው ስፍራ ነው) ልብስ መመኘቱ ነበረ—7፡21፡-

1. መንፈስ ቅዱስን የዋሹት ሐናንያና ሰጲራ ኃጢአትን ያደረጉት በተመሳሳይ መርህ ነው—ይህ የባቢሎን መርህ ነው፣ እርሱም ግብዝነት ነው—ሐዋ. 5፡1-11፤ ራእ. 17፡4፣ 6፤ ማቴ. 23፡13-36፡-
   ሀ. ጌታን በጣም አይወዱትም ነበረ፣ ነገር ግን ጌታን እጅግ በጣም እንደሚወዱት አድርገው ለመታየት ፈለጉ፤ እያስመሰሉ ብቻ ነበረ፤ የእግዚአብሔር ልጆች በሰው ፊት ከማስመሰል መዳን አለባቸው።
   ለ. ሁሉን ነገር በደስታ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ አልፈለጉም፣ በሰው ፊት ግን ሁሉንም እንዳቀረቡ አስመሰሉ፣ እውነተኛ ሁኔታችንን የማይመጥን ልብስን በለበስን ጊዜ ሁሉ፣ በባቢሎን መርህ ውስጥ ነን—6፡1-6፤ 15፡7-8።
2. ከሰው ክብር ለመቀበል በሐሰት የሚደረግ ነገር በሙሉ የሚደረገው በሙሽራይቱ መርህ ሳይሆን በጋለሞታይቱ መርህ ነው፤ የውሸት መስጠትና የውሸት መንፈሳዊነት ኃጢአቶች ናቸው፣ እውነተኛ አምልኮ ግን በመንፈስና በእውነት ነው፤ እግዚአብሔር እውነተኛ ሰዎች ያድርገን—ራእ. 17፡4-5፤ 19፡7-9፤ ሉቃ. 12፡1፤ 1 ቆሮ. 2፡9-10፤ 2 ቆሮ. 2፡10፤ 5፡14-15፤ ዮሐ. 4፡23-24።
3. "ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" (1 ሳሙ. 16፡17)፤ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችን እንደ ውድ መዝገብ ከያዝነው (መዝ. 119፡11) እና ክርስቶስ በልባችን ቤቱን እንዲሠራ ከፈቀድንለት (ኤፌ. 3፡16-17)፣ የልባችን መልካም መዝገብ ይሆናል፣ በልባችንም ሞልቶ ከተትረፈረፈው እርሱን እንደዚህ ድንቅ፣ መልካም ውድ መዝገብ ለሌሎች ማደል እንችላለን (ሉቃ. 6፡44-45)።

**III. እስራኤል ኃጢአታቸውን፣ የአካንን ኃጢአት ካስወገዱ በኋላ (ኢያ. 7፡11-12፣ 20-21)፣ በጋይ ላይ ድል ተቀዳጁ (8፡1-35)፣ ከዚያ በኋላ ግን የእስራኤል ልጆች እንዴት በገባዖን ሰዎች እንደታለሉ የሚናገር ዘገባ አለ (9፡1-27)፡-**

ሀ. የገባዖን ሰዎች ኤዊያዊያን (ቁ. 3፣ 7፣ 11፡18-19)—ዲያብሎሳውያንና ከአጋንንት ጋር የተዋሐዱ ስለነበሩ በእስራኤል መጥፋት ከነበረባቸው በከነዓን ምድር ከነበሩ አሕዛብ መካከል አንዱ ነበሩ (ዘዳ. 7፡2፣ 9፡4-5፤ 18፡9-14)፤ የገባዖን ነዋሪዎች በተንኮላቸው እስራኤልን አሳቱት (ኢያ. 9፡3-14)።

ለ. እስራኤል ኢያሪኮን እና ጋይን ማሸነፋቸውን ሰምተው ስለነበር፣ እስራኤል በሕይወት እንዲኖሩ እንዲፈቅዱላቸው ከእስራኤል ጋር ሰላም ማድረግና ኪዳን መግባትን ፈለጉ፤ መልእክተኞች እንደሆኑና ከሩቅ እንደመጡ ባማስመሰል መጡ፤ ወደ ጌልጌላ ሰፈር ወደ ኢያሱ ሄደው ለእርሱና ለእስራኤል ሰዎች "ከሩቅ አገር መጥተናል...እኛ ባሪያዎቻችሁ ነን፤ አሁንም ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድርጉ" (ቁ. 6፣ 11)።

ሐ. ኢያሱ 9፥14 የእስራኤል ልጆች ለምን በገባዖን ሰዎች እንደተታለሉ የሚያሳየን በመጽሐፍ ቅዱስ ያለ በጣም ኃይለኛ ክፍል ነው—“እግዚአብሔርንም አልጠየቁም”፤ ከዚህም የተነሣ፣ ኢያሱ ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ፣ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (ቁ. 15)፦

1. የእስራኤል ልጆች የተታለሉት ባሏን እንደረሳች ሚስት ስለነበሩ ነው፤ መላው መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ፍቅር፣ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሕዝብ እንዴት እንደሚያጫቸውና በመጨረሻ እንደሚያገባቸው የሚያሳይ ዘገባ ነው (ዘፍ. 2፥21-24፤ መኃ. 1፥2-4፤ ኢሳ. 54፥5፤ 62፥5፤ ኤር. 2፥2፤ 3፥1፣ 14፤ 31፥32፤ ሕዝ. 16፥8፤ 23፥5፤ ሆሴ. 2፥7፣ 19፤ ማቴ. 9፥15፤ ዮሐ. 3፥29፤ 2 ቆሮ. 11፥2፤ ኤፌ. 5፥25-32፤ ራእ. 19፥7፤ 21፥2፣ 9-10፤ 22፥17)።
2. መጽሐፍ ቅዱስ እኛ፣ እንደ የእግዚአብሔር ምርጦች፣ ሚስቱ መሆናችንን እና በእኛ እና በእርሱ መካከል በጋራ በሆነ ፍቅር የጋብቻ ጥምረት መኖር እንዳለበት ያሳየናል፤ ስለዚህ፣ አጽናፍ-ዓለም የጋብቻው ስፍራ፣ ባል የሆነው በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ፣ ከተዋጀው፣ ዳግም ከተወለደው፣ ከተቀደሰው፣ ከታደሰው፣ ከተለወጠው እና ከከበረው ሦስት ክፍል ካለው ሰው ጋር በጋብቻ እየተጋጠመ ያለበት ስፍራ ነው፤ በመጨረሻ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር የእግዚአብሔር ምርጦች ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መጠናቀቅ፣ ለዘላለም አጽናፍ-ዓለማዊቷ ሚስት በሆነችው በአዲቱ ኢየሩሳሌም ይጠናቀቃል—21፥9-10፤ 22፥17።
3. ሚስት ባሏን በፍጹም መተው የለባትም፤ ይልቁንም ሁልጊዜ በእርሱ ላይ መደገፍና ከእርሱ ጋር አንድ መሆን አለባት፤ የገባዖን ሰዎች ወደ እስራኤል ሲመጡ፣ እንደ ሚስት እስራኤል ወደ ባሏ መሄድና ምን ማድረግ እንዳለባት ከእርሱ ማረጋገጥ ነበረባት—ኢያ. 9፥14።
4. ጌታን እንደሚወዱ እና የእርሱ ድል-ነሺ ሙሽራ ክፍሎች መሆን እንደሚፈልጉ አማኞች፣ ስለሚያጋጥመን እያንዳንዱ ችግር እግዚአብሔርን ማማከር አለብን፤ ሁሉንም ጉዳይ ወደ ጌታ ማምጣትና ነገሮችን በእርሱ ፊትና ከእርሱ ጋር ኅብረት በማድረግ በጥንቃቄ ማሰብ፣ መመርመር እና ማወቅ ያስፈልገናል፦
   ሀ. በዚህ ረገድ፣ እያንዳንዱ አማኝ ጌታ እንዲወስንለት በመፍቀድ ጌታን ሳይገናኝ እና ከእርሱ ጋር ሳይማከር፣ የራሱ ሃሳብ እስከማይኖረው ድረስ፣ በራሱ መወሰን እስከማይችል ድረስ፣ ወይም ከሚያጋጥመው ነገር ጋር በተገናኘ ምንም አይነት እርምጃ መውሰድ እስከማይችል ድረስ ደካማ መሆን አለበት፤ የክርስቲያን ጣፋጩ ኑሮ ይህ ነው—2 ቆሮ. 12፥9-10።
   ለ. በሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ከማድረግ፣ ሁሉን ነገሮች ከእርሱ ጋር ከመወያየት እና ሁሉን ነገር እርሱ እንዲያደርገው፣ በሁሉ ነገር እንዲናገር እና እያንዳንዱን ውሳኔ እርሱ እንዲወስን ከመፍቀድ ውጭ አማራጭ የለንም፤ ክርስቲያን በሁሉም ጊዜና በሁሉ ጉዳይ በአንድ በሌላ ማንነት—በእግዚአብሔር—ላይ መደገፉ የከበረ ነገር ነው—ፊልጵ. 4፥6-7፤ ምሳ. 3፥5-6፤ ኤር. 17፥7-8፤ 2 ቆሮ. 1፥8-9፤ መዝ. 62፥8፤ መዝ. 102. ርእስ እና ቁ. 7።
5. እግዚአብሔር የማታውቁትን መንገድ እንድትወስዱ ከመራችሁ፣ “ይህ ከእርሱ ጋር በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ልውውጦች እንዲኖራችሁ ይገፋችኋል፤ ይህም በእናንተ እና በእርሱ መካከል ዘላለማዊ መታሰቢያ ያለውን ጉዞ ያመጣል”—*The Collected Works of Watchman Nee,* vol. 7 ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገፅ 1144 የተወሰደ።
6. እስራኤል የባሏን ምክር ያለመፈለጓ ውጤት ይህች ኢ-ጥገኛና ግለሰባዊ የሆነችው ሚስት መታለሏ እና ምንም ዓይነት መከላከያና ጥበቃ የሌላት መሆኗ ነበረ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ከዚህ ዘገባ፣ እንደ ጌታ ሚስት፣ ሁልጊዜ በእርሱ ላይ በመደገፍ እና ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን ከእርሱ ጋር አብሮ-መኖር እንዳለብን መማር ያስፈልገናል፤ የኢያሱ 9 ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ይህ ነው።

© 2021 Living Stream Ministry